ወርሃዊ ሪፖርት 001
መጋቢት 2017 ዓ.ም



# እንደራሴ

የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ክራሞት

## ጥራዝ 1

ወርሃዊ ሪፖርት 001
መጋቢት 2017 ዓ.ም

እንደራሴ በብሪጅ ሪሰርች እና ኢኖቬሽን በየወሩ እየተዘጋጀ ይቀርባል።


research@biridge-et.org
bridge-et.org

PARLIAMENTS PEACE POLICY

# እንደራሴ
# የኢትዮጲያ ፓርላማዊ ክራሞት

# Enderase
# Ethiopian Parliamentary Review

ይህ የመጋቢት ወር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ክራሞት እትም፣ እንደራሴዎች ካከናወናቸው አበይት ክንውኖች ከምክር ቤቱ ተልኮዎች የሆኑትን አራት ጉዳዮች አካቷል፡ ሕግ ማውጣት፣ ውክልና፣ የአስፈጻሚ አካላት ቁጥጥር እና የፓርላማ ዲፕሎማሲ። የአስፈጻሚ አካላት ቁጥጥር ተግባራት ውስጥ የሚካተተው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አህመድ በፌዴራል መንግስት የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያ ግማሽ ዓመት አፈፃፀምን መነሻ በማድረግ ከምክር ቤቱ ለተነሱት ጥያቄዎች መልስና ማብራሪያ መስጠታቸው ከዚህ ወር ዋና ዋና ተግባራት አንዱ ሲሆን፤ ቀዋናው ሲሆን፤ እትሙ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት፣ ከተለያዩ የዜና ማሰራጫዎችና ተቋማት መረጃዎችን አሰባስቦ እና ተንትኖ በዚህ መልክ አቅርቧል።




## 1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማ

ይህ የመጋቢት ወር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ክራሞት እትም፣ እንደራሴዎች ካከናወናቸው አበይት ክንውኖች ከምክር ቤቱ ተልኮዎች የሆኑትን አራት ጉዳዮች አካቷል፡ ሕግ ማውጣት፣ ውክልና፣ የአስፈጻሚ አካላት ቁጥጥር እና የፓርላማ ዲፕሎማሲ። የአስፈጻሚ አካላት ቁጥጥር ተግባራት ውስጥ የሚካተተው የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አህመድ በፌዴራል መንግስት የ 2017

በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ በሠጡት ማብራሪያ፣ መንግስት በዐሥር ዓመታት የሚተገበር የልማት ዕቅድ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ወደ ሥራ መግባቱን ገልጸዋል።አስታውሰው እንደራሴዎቹ በአገሪቷ ኢኮኖሚ ዘሪያ ካነሷቸው ጥያቄዎች መካከል፣ በአምራች ዘርፉ ያለውን የጥሬ ዕቃ የአቅርቦት ችግሮች፣ የዐሥር ዓመቱን ዕቅድ፣ የነዳጅ ድጎማ እና ሕገ-ወጥ ሽያጭ፣ ተጀምረው የተጓተቱ አገራዊ ፕሮጀክቶች

እንዲኹም የአፈር ማዳበሪያ ሥርጭት መዘግየትና በመሳሰሉት ጉዳዮች መልስ ሰጥተዋል ፡፡

ጠቅላይ ሚንስትሩ ባለፉት ስምንት ወራት በዋና ዋና የማክሮ-ኢኮኖሚ አመላካቾች ታላላቅ ስኬቶች ተመዝግበዋል ብለዋል፡፡ የዕዳ ሽግሽግ ለማድረግ ሲሰራ መቆየቱን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የኢትዮጵያ አቋም ዕዳ እንዲሰረዝ ማድረግ መኾኑንም ገልጸዋል፡፡ በተያዘው የበጀት ዓመቱ ቀሪ ወራት ይኽን ስኬት ማጠናከር ከተቻለ፣ ከ8 ነጥብ 4 በመቶ በላይ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብ እንችላልን ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ገቢው ሙሉ በሙሉ ወጪውን መሸፈን ባይችልም መጠነኛ መሻሻሎች መታየታቸውን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ አኹንም ኢትዮጵያ እየሞከረች ያለችው ከጥቅል አገራዊ ምርቷ (Gross Domestic Product) ሰባት በመቶ ገደማ ገቢ ለመሰብሰብ መኾኑን አስታውቀዋል። በሚቀጥሉት አራት ወራት አኹን ባለው ሂደት ከቀጠለ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ የውጭ ንግድ ስኬት ይመዘገባል ብለዋል፡፡

| 2016/2017 (እስከ መጋቢት) | |
|---|---|
| የኢኮኖሚ እድገት | 8.1% (ቀሪ ወራት ግምት › 8.4%) |
| ለነዳጅ እና ለአፈር ማዳበሪያ ድጎማ | 156 ቢሊየን ብር |
| የአገር ውስጥ ገቢ | › 580 ቢሊዮን ብር |
| የዕዳ ሽግሽግ | 3.5 ቢልዮን ዶላር |
| ለውጭ ገበያ | 4.5 ቢሊዮን ዶላር |
| በአገር ውስጥ እና በውጭ አገራት የሥራ ስምሪት | 3 ሚሊየን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድሎችን ተፈጥረዋል |

## ጠቅላይ ሚንስትሩ የታጠቁ ሃይሎችን “አያዋጣም ተዉት” ብለዋል።

ከተለያዩ ታጣቂዎች ጋር ይደረጋሉ ስለሚባሉ ድርድሮችም ሲያወሱ፣ መንግስታቸው ለሰላም እጁ የተዘረጋ መሆኑን በማንሳት፣ በድርድር እና በሰለጠነ መንገድ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ሁሌም ቢሆን ዝግጁ መሆኑንም ጠቅሰዋል። ከዚያ ባለፈም፣ ዛሬም ቢኾን በአክራሪዎች፣ በጽንፈኞች እና በታጣቂዎች የሚገደሉ ዜጎች እንዳሉ በማንሳት፣ መንግስት በብቸኝነት ሀይል የመጠቀም ስልጣን ያለው በመሆኑ ዘላቂ ሰላምን እና ፍትሓዊነትን ለማረጋገጥ ወደ ይህን ሃይል ሊጠቀም እንደሚችል ተናግረዋል፤ የሚዋጋቸው ሰዎች “አትማሩ፤ አትታከሙ፤ አትረሱ ከሚሉ ጋር ነው” ብለዋል፡፡

“የምንዋጋቸው መድኃኒት አውጥተው የሚደፉ፤ ማዳበሪያ እንዳይደርስ የሚያደርጉ፣ ነገር ግን ለሕዝብ እንታገላለን ባይ ናቸው” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ነውጠኛ ነፃ አውጭ ነን ባዮች “መጀመሪያ ተጎጂ የሚያደርጉት የራሳቸውን ሕዝብ ነው” ብለዋል፡፡

## ቀይ ባሕር

ከተለያዩ ታጣቂዎች ጋር ይደረጋሉ ስለሚባሉ ድርድሮችም ሲያወሱ፣ መንግስታቸው ለሰላም እጁ የተዘረጋ መሆኑን በማንሳት፣ በድርድር እና በሰለጠነ መንገድ የሚነሱ ችግሮችን ለመፍታት ሁሌም ቢሆን ዝግጁ መሆኑንም ጠቅሰዋል። ከዚያ ባለፈም፣ ዛሬም ቢኾን በአክራሪዎች፣ በጽንፈኞች እና በታጣቂዎች የሚገደሉ ዜጎች እንዳሉ በማንሳት፣ መንግስት በብቸኝነት ሀይል የመጠቀም ስልጣን ያለው በመሆኑ ዘላቂ ሰላምን እና ፍትሐዊነትን ለማረጋገጥ ወደ ይህን ሃይል ሊጠቀም እንደሚችልተናግረዋል፤ የሚዋጋቸው ሰዎች “አትማሩ፤ አትታከሙ፤ አትረሱ ከሚሉ ጋር ነው” ብለዋል፡፡ “የምንዋጋቸው መድኃኒት አውጥተው የሚደፉ፤ ማዳበሪያ እንዳይደርስ የሚያደርጉ፣ ነገር ግን ለሕዝብ እንታገላለን ባይ ናቸው” ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ነውጠኛ ነፃ አውጭ ነን ባዮች “መጀመሪያ ተጎጂ የሚያደርጉት የራሳቸውን ሕዝብ ነው” ብለዋል፡፡

## 2. የምክር ቤቱ የሕግ የማውጣት ተግባሮች

በመጋቢት ወር ምክር ቤቱ ሁለት አዋጆችን ያጸደቀ ሲሆን፤ አንድ ረቂቅ አዋጅ ለሚመለከተው የቋሚ ኮሚቴ ለዝርዝር ጥናት እንዲላክ ተደርጎ፣ ሦስት አስረጂ መድረኮች በረቂቅ ሕጎች ላይ ተደርገዋል፡፡

### 2.1 የጸደቁ ሕጎች

የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በወርሃ መጋቢት ካፀደቃቸው ሕግጋት አንዱ፣ የተመሠከረላቸው የሒሳብ ባለሙያዎች ኢንስቲቲዩት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ነበር፡፡ በ 19ኛው መደበኛ ስብሰባ ምክር ቤቱ የቀረበለትን ረቂቅ አዋጅ መርምሮ  አዋጅ ቁጥር 1372/2017 በማድረግ በሙሉ ድምጽ አጽድቋል። የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ደሳለኝ ወዳጄም፣ ሪፖርት እና የውሳኔ ሐሳቡን ለምክር ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን አዋጁ በኢትዮጵያ ዓለም ዓቀፍ የተመሠከረላቸው ባለሙያዎችን ለማፍራት አቅም የሚፈጥር መሆኑን አብራርተዋል። የኢፌዲሪ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶኤታው ኢዮብ መኮንን ዓለም ዓቀፋዊ እና አህጉራዊ ተሞክሮዎችን መሠረት ያደረገ መሆኑን ጠቀመው፣ የፋይናንስ አቅምን ለማሳደግ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የሚያጠናክሩየሃሳብ አያያዝ፣ ኦዲትና የፋይናንስ መረጃዎችን የማስተዋወቅ ሚናው ከፍ ያለ እንደሚሆን አብራርተዋል። በተጨማሪም ምክር ቤቱ አሁን በሥራ ላይ ያለውን የፌደራል መንግሥት በክልሎች ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ በ1995 ዓ.ም የወጣውን አዋጅ አሻሽሏል፡፡

በም/ቤቱ የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትርና የፍትህ ሚኒስትር ወ/ሮ ሃና አርያስላሴ አዋጁ የጊዜያዊ አሥተዳደር የመቆያ ጊዜ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚሻሻል ግልፅ አሰራር እንደሚዘረጋ አስረድተዋል፡፡፡፡ ምክር ቤቱ፣ መጋቢት 23 ቀን 2017 ዓ.ም. ባካሄደው 22ኛ መደበኛ ስብሰባው፣ የቀረበለትን ይኸንኑ የማሻሻያ አዋጅ ያፀደቀው በኹለት ድምጸ-ተዐቅቦና በአብላጫ ድምጽ ሲሆን፤ ነባሩን አዋጅ ቁጥር 359/1995ን ተክቶ “የፌደራል መንግሥት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣ  ማሻሻያ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1373/2017” በሚል አፅድቆታል፡፡ የአዋጁ ማሻሻያ የውሳኔ ሐሳብ ያቀረቡት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ዶ/ር ተስፋዬ በልጅጌ በትግራይ ክልል ጊዜያዊ አሥተዳደርን እንደምሳሌ በማንሳት የአሥተዳደሩ ዘመን በቀደመው አዋጅ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ክልሉ ካለው ነባራዊ ኹኔታ ጋር የማይጣጣም ሆኖ በመገኘቱ በአዋጁ አተገባበር ወቅት ክፍተት ፈጥሯል ሲሉ የማሻሻያውን አስፈላጊነት የገለጹ ሲሆን፤ ዝርዝር ሃሳቦችን በገጽ 12 ይመልከቱ፡፡

የተወካዮች ምክር ቤት መጋቢት 9 2017 ዓ.ም. ባካሄደው 20ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢትዮጲያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 16/2017 ለዝርዝር እይታ በሙሉ ድምጽ ለውጭ ግንኙነት እና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል፡፡ በምክር ቤቱ የመንግስት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር የሆኑት የተከበሩ ዶ/ር ተስፋዬ በልጅጌ፣ ረቂቅ አዋጁን አስመልክቶ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በማብራሪያው "የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር የቅድመ-አደጋ፣ የአደጋ ወቅት እና ድህረ-አደጋ ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ የፌደራል እና የክልል አሥተዳደር ተቋማት የውስጥ አቅም ለመገንባት" አዋጁ ማስፈለጉን አንስተዋል፡፡ በረቂቅ አዋጁ ማብራሪያ ላይ በቅድመ አደጋ፣ በአደጋና በድኅረ አደጋ ወቅቶች ለሚወሰዱ የአደጋ ሥጋት ቅነሳ፣ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የሚሆን የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ምላሽ ፈንድ የሚያቋቁም ሲሆን፤ ፈንዱ ከሠራተኞች ደመወዝ ላይ ከሚቆረጥለት ገቢ በተጨማሪ ከባንኮችና ከተለያዩ የፋይናንስ እና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች፣ ከበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ከፌዴራል መንግሥት፣ ከሁለቱ ከተማ አስተዳደሮች ከጠቅላላው ዓመታዊ በጀት በድርሻ እንደሚሰበሰብም ተብራርቷል።

## 2.3 የአስረጂ መድረኮች

ምክር ቤቱ መጋቢት 2017 ዓ.ም በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን እንዲሁም የኢትዮጵያ የኮንስትራክሽን ኢንድስትሪ አሰላሳይ ግሩፕ ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆች ላይ ሦስት የአስረጂ መድረኮችን አካሂዷል።

መጋቢት 15 ቀን ለውሃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እና የከተማ፣ መሠረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅ ማስረጃ ነባሩ አዋጅ ቁጥር 513/1999 ከከተሞች መስፋፋት ጋር በተያያዘ የሚመነጨው የቆሻሻ ማመንጨት መጠን መጨመርን ተከትሎ እና ነባሩ ህግ ከ18 ዓመታት በፊት የወጣና የገጠሩን የሀገሪቱን ክፍል ብዙ ትኩረት ያልሰጠ በመሆኑን የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዋና ዳይሬክተር ሌሊሴ ነሜ (ኢ/ር) እና የሥራ ባልደረቦቻቸው ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሰው መጋቢት 17ን ለውጭ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበው የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ረቂቅ አዋጅ ሽግግርን መፍጠር ተቋማዊ ቁመናን ማጠናከርና የፋይናንስ አቅምን ለማጎልበት መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) እና የሥራ ባልደረቦቻቸው አብራርተዋል፡፡

በመጋቢት 29 ለከተማ፣ መሰረተ ልማት እና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበው ማስረጃ የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ አሰላሳይ ግሩፕ (Ethiopian Construction Industry Think Thank Group) ማቋቋሚያ ረቂቅ ደንብን ለማዳበር ሲሆን፤ የኮንስትራክሽን ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ ችግር ፈቺ ጥናቶችን የሚያካሂድ አሰላሳይ /ቲንክ ታንክ/ ግሩፕ መቋቋም አስፈላጊና ለኮንስትራክሽን ዘርፉ ጠቃሚ መሆኑን የከተማና መሰረተ ልማት ሚንስቴር ሚንስትር ዴኤታ አቶ የትምጌታ አስራት ገልጸዋል፡፡

[1] የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ "ምክር ቤቱ የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ መራ" https://www.hopr.gov.et/-/ምክር-ቤቱ-የኢትዮጵያ-የአደጋ-ስጋት-ስራ-አመራር-ረቂቅ-

[1] ሪፖርተር "የመንግሥትና የግል ሠራተኞች ከደመወዛቸው ለአደጋ ሥጋት ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚያስገድድ ረቂቅ አዋጅ ቀረበ" https://www.ethiopianreporter.com/139426/

[1] የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ "በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ረቂቅ አዋጅ ላይ የአስረጂ መድረክ ተካሄደ" https://web.facebook.com/share/p/14tC8C6ZSd/


[1] የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ "ረቂቅ አዋጁ ሀገሪቱን ከተረጅነት እና ህዝብንም ከጥገኝነት አስተሳሰብ ሊያላቅቅ እንደሚችል ተገለፀ" https://web.facebook.com/share/p/1ANTRpQ4wu/


## 3. የውክልና ሥራ

የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች ከዋና ዋና ሥራዎች አንዱ የሆነው የውክልና ሥራ ሲሆን፤ እንደራሴዎች የመረጧቸውን ወይም የወከሏቸውን መራጮች በየምርጫ ወረዳቸው ሄደው ማወያየት እና ጥያቄዎቻቸውን መስማት በዓመት ሁለት ጊዜ ከሚያደርጊቸው ተግባራት አንዱ ነው፡፡ በመጋቢት ወርም ከየካቲት ወር በቀጠለ በርካታ እንደራሴዎች ወደየ ምርጫ ወረዳቸው በመሄድ መራጮቻቸውን አወያይተዋል፡፡

በመጋቢት ወር 2017 ዓ.ም ከ 40 በላይ በሚሆኑ መድረኮች /የመራጭ -ተመራጭመድረኮች/ በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ደቡብ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ሶማሌና ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልሎች የተካሄዱ ሲሆን ሰፋ ያሉ አገራዊና አካባቢያዊ አጀንዳዎች በጥልቀት ተዳስሰዋል፡፡

## የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት




[1] ሪፖርተር፤ "የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ቀጥተኛ መልስ የታጣላቸው ውስብስብ ችግሮች አያጋጠሙት መሆኑ ተነገረ።" https://www.ethiopianreporter.com/140101/

በተደጋጋሚ ከተነሱት ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል የሴቶች ህገ-መንግስታዊ መብቶችና በሴቶችና ህፃናት ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ቀዳሚውን ስፍራ ይዘዋል። በኦሮሚያ /ምዕራብ ወለጋ፣ ሰሜን ሸዋ/፣ ወላይታ፣ አማራ/አዊ/ እና ዳውሮ ዞኖች በተካሄዱት ውይይቶች የሴቶችን መብትና ጥቅም ማስከበር፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ፣ ጥቃቶችን በጋራ መከላከልና ጎጂ ልማዶች ተነስተዋል። በተለይ ሴቶች በአገራዊ ምክክር ላይ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች አስፈላጊነት ላይ አጽንኦት ተሰጥቷል።

በተመሳሳይ መልኩ የሰላምና የፀጥታ ጉዳዮች እንዲሁም የመሠረተ ልማት ዝርጋታ መጓተት በበርካታ ውይይቶች ላይ ጎልተው ታይተዋል። በኦሮሚያ /ሰሜን ሸዋ፣ ቡኖበደሌ/፣ ሶማሌ፣ ደቡብ (ወላይታ፣ አሪ) እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች በተካሄዱት መድረኮች የሰላም እጦት የሚያስከትለውን ችግሮች የወደሙ ትምህርት ቤቶችን የጤና ተቋማት መልሶ ግንባታ የውሃ አቅርቦት መቋረጥ የባንክ አገለግሎቶች እጥረትና ሕገወጥ የዳንበር ንግድን መከላከል ላይ ውይይት ተደርጓል። ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን የፀጥታ አካላትና ህዝብ በቅንነት እንዲሰሩ ጥሪ የቀረበ ሲሆን የፍትህና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ አስፈላጊነትም አጽኖት ተሰጥቶበታል።

ከእነዚህ አንኳር ጉዳዮች በተጨማሪ የመራጮችና የተወካዮች ውይይቶች፣ የመልካምአስተዳደር ችግሮች፣ የተፈናቃዮች ጉዳይና ወደቀያቸው የመመለሳቸው ሁኔታ፣ የልማት ፕሮጀክቶች አፈፃፀም መጓተት፣ የመንገድ ሥራዎች፣ የንፁህ የመጠጥ ውሀ አቅርቦት እጥረት፡ የአምቡላንስና የመድሀኒት እጥረት፣ የመብራትና የኔትወርክ አገልግሎት አለመኖር፣ የትራንስፖርት ችግሮች፣ የሥራ አጥነት፣ የኑሮ ውድነት፣ የማዳበሪያ ዋጋ ንረት፡ የግብርና ግብዓት አቅርቦት ውስንነት፣ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ፣ የአረንጓዴ አሻራና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንደሁም ከልማት ጋር የተያያዘ የታክስ ክፍያዎች መዘግየት የመሳሰሉ በርካታ አጀንዳዎች ተዳሰሰዋል፡፡

## 4. የአስፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር

የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንደራሴዎች ከዋና ዋና ሥራዎች አንዱ የሆነው የአስፈጻሚ ተቋማት ቁጥጥር ሲሆን፤ በዚህ ረገድ የአስፈጻሚ ተቋማትን ሪፖርት መስማት፣ የተቋማት እና የመስክ ጉብኝት ናቸው፡፡

## 4.1 የአስፈጻሚ ተቋማት ሪፖርቶች

የተለያዩ የመንግስት ተቋማት ለተለያዩ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቋሚ ኮሚቴዎች ከ 8-9 ወራት የሚደርስ የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት አቅርበዋል። መጋቢት 15 ቀን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግስ ለልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀረበ ሲሆን የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ ስራ አስፈጻሚ ብሩክ ታዬ (ዶ/ር) በግማሽ አመቱ 901 ቢሊዮን ብር ገቢ ማመንጨት ተችሏል ያሉሲሆን 14 ነጥብ 5 ቢሊዮን ብር የመንግስት ትርፍ ድርሻ ለገንዘብ ሚኒስቴር ገቢ ተደርጓል ሲሉ በሪፖርታቸው ገልፀዋል፡፡
መጋቢት 25 ቀን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የ 8 ወራት አፈፃፀም ሪፖርቱን ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል። ሪፖርቱን ያቀረቡት የባንኩ ፕሬዚዳንት አቤ ሳኖ ከሌሎች ጉዳዮች በተጨማሪ ባንኩ ባለፉት ስምንት ወራት ብቻ 264 ነጥብ 65 ቢሊየን ብር ብድር ለደንበኞች ማቅረቡን ገልጸው÷ ከተሰጠው ብድር 88 ነጥብ 2 በመቶ ለግሉ ዘርፍ የተሰጠ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡ መጋቢት 24 ቀን የትምህርት ሚኒስቴር የ 12ኛ ክፍልውጤት ዝቅተኛ የመሆን ምክንያቶችን አስመልክቶ ያጠናውን ጥናት ለሰው ሀብት፣ ልማት፣ ስራ ምርትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል። ጥናቱን የትምህርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ብርሃኑ ነጋ (ፕሮፌሰር) ያቀረቡ ሲሆን ለተማሪዎች ውጤት ማሽቆልቆል እና ውድቀት ባለድርሻ አካላት በብልሹ አሰራር ተባባሪ መሆናቸውን፣ 8ኛ ክፍል ደርሰው ማንበብ የማይችሉ ተማሪዎች እንደነበሩ፣ ፈተናው ሕብረተሰቡ የደረሠበትን የሞራል ስብራት እና ውድቀት በማሳየቱና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወላጆች ለልጆቻቸው ልዩ ትኩረት መስጠታቸውን በመግለጽ፤ ችግሩን ለመፍታት የመምሕራንን የኑሮ ሁኔታ ማሻሻል ቀልፍ ጉዳይ መሆኑና እንደ ሀገር ከ 100 ሺህ በላይ የመምሕራን እጥረት እንዳጋጠመም ገልጸዋል፡፡
መጋቢት 24 ቀን የማዕድን ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የስምንት ወራት የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቱን ለኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አቅርቧል፡፡ የአፈፃፀም ሪፖርቱን ያቀረቡት ሚንስትሩ ክቡር ኢንጅነር ሀብታሙ ተገኝ፤ዚህ ቀደም በማዕድን ዘርፍ ላይ ትልቅ የተመዘገበው 800 ሚሊዮን ዶላር ሲሆን በዚህ ስምንት ወራት ውስጥ 1.88 ቢሊየን ዶላር የውጭ ምንዛሬ አስመዝግበናል፤ ከዚህ ውስጥ ወርቅ ትልቁን ድርሻ ይይዛል ብለዋል፡፡

[1] የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “የልማት ድርጅቶች የሕዝብ ጥያቄዎችን የዕቅዳቸው አካል ሊያደርጉ እንደሚገባ ተመላከተ። ” https://web.facebook.com/share/p/1HM3edL1ND/
[1] ኢትዮ ኤፍ ኤም 107.8፤ “የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለፉት ስምንት ወራት ብቻ 264 ነጥብ 65 ቢሊየን ብር ብድር ለደንበኞች ማቅረቡን አስታውቋል።” https://ethiofm107.com/2025/04/02/የኢትዮጵያ-ንግድ-ባንክ-ባለፉት-ስምንት-ወ/
[1]የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “የትምሕርት ዘርፍ  የትምሕርት ሚኒስቴር ጉዳይ ብቻ አይደለም።” https://web.facebook.com/share/p/1F6ikd7smy/
[1] የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “ቋሚ ኮሚቴው፣ ከአገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ውስጥ አንዱ የሆነው የማዕድን ዘርፍ ይበልጥ ውጤታማ እንዲሆን በትኩረት መስራት እንደሚገባ አሳሰበ።” https://web.facebook.com/share/p/12J3Ghbp2p1/

መጋቢት 25 ቀን በኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የሬድዮና የቴሌቪዥን፣ የዜናና ወቅታዊ ጉዳዮች አግልግሎት አሰጣጥ አፈጻጸም ውጤታማነት በተመለከተ ከ2013 እስከ 2015 ዓ.ም ድረስ ያለውን የኦዲት ሪፖርት ለመንግስት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የቀረበ ሲሆን የፌደራል ዋና ኦዲተር ክብርት ወ/ሮ መሰረት ዳምጤ ተቋሙ ከነበረበት ሁኔታ መሰረታዊ ለውጥ እንደታየበት ተናግረዋል፡፡

የኢቢሲ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ጌትነት ታደሰም በለውጡ የተገኘውን አጋጣሚ በመጠቀም ህብረተሰቡ በተለያዩ መልኩ ሀሳቡን የሚሰጥበት ሁኔታ የተመቻቸ መሆኑን እና ተቋሙን የሀሳብ ተቋም ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል፡፡

## 4.2 የተቋማትና የመስክ ጉብኝት

በወርሃ መጋቢት 2017 ዓ.ም እንደራሴዎቹ ወደ ወከሏቸው መራጮቻቸው ወይይት ያደርጉ ዘንድ ከመሄዳቸው ባለፈ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎችና የምክር ቤቱ ኃላፊዎች በመላው ኢትዮጲያ ወደ 32 የሚሆኑ የመስክ ጉብኝትን ጨምሮ የተለያዩ የፌዴራል እና የክልል ተቋማትን አኹናዊ ኹኔታዎችን ጎብኝተዋል፡፡

### 4.2.1 የተቋማት ጉብኝት

ከተቋማት ጉብኝቶች ውስጥ ማሳያ ሊሆኑ ከሚችሉት መካከልም፣ የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ይገኝበታል፡፡ መጋቢት 3 ቀን 2017 ዓ.ም.፣ በምክር ቤቱ የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት በማተሚያ ቤቱ በተደረገው ጉብኝት፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና ማሽነሪዎችን ወደ ዘርፉ በማስገባት ተቋሙን ተወዳዳሪ ማድረግ መቻሉ ተነግሯል፡፡ የማተሚያ ቤቱ ዋና ሥራ አሥፈጻሚ ሽታሁን ዋለ፣ የኅትመት ዘርፉ ተለዋዋጭ ቴክኖሎጂ ያለበት መሆኑን ለኮሚቴው አባላት ጠቀመው፣ ድርጅቱ የሚጠቀምባቸው አብዛኛዎቹ የኅትመት መሣሪያዎች ግን ከዘመኑ ጋር እንደማይሄዱም አብራርተዋል የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንም፣ በተጠቀሰው ወር በእንደራሴዎቹ የተጎበኘ ሌላኛው የፌዴራል መንግስቱ ተቋም ነበር፡፡ መጋቢት አጋማሽ ላይ፣ በእንደራሴዎቹ የሰው ሀብት ልማት፣ ሥራ ስምሪት እና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢው ነገሪ ሌንጮ በተመራው ይኸው የኮሚሽኑ ጉብኝት፣ የተቋሙ የማሻሻያ ሥራዎች ምን ላይ እንዳደረሱ ኮሚቴው ገምግሟል ተብሏል፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር መኩሪያ ኃይሌ፣ ሲቪል ሰርቪሱ ኢትዮጵያን በሚመጥን ደረጃ እንዲሆን በርካታ ተግባራት መከናወናቸውን ጠቅሰው፣ በዚኽም የተደራጀ መረጃ አያያዝን የተከተለ ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን ላገኟቸው የኮሚቴው አባላት አብራርተውላቸዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴውም፣ የተቋሙን የቢሮ አደረጃጀት፣ የተለያዩ አገራዊ ስያሜ ያላቸውን ዘመናዊ የአሥተዳደር ፍርድ ቤት የችሎት እና የሥልጠና አዳራሾችን ጨምሮ፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት አሰጣጥ አኹናዊ ኹኔታን መመልከቱን የምክር ቤቱ መረጃ ያሳያል፡፡
የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክም፣ በወርሃ መጋቢት ከተጎበኙት ተቋማት መካከል የሚጠቀስ ነው፡፡ በምክር ቤት የመንግስት ልማት ድርጅቶች ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አማካኝነት በተካሄደው ይኸው ጉብኝት፣ ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ከገጠመው ፈታኝ ኹኔታ በማገገም ዐሥር ሺህ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠሩን እና ለውጭ ገበያ በሚያቀርባቸው ምርቶችም ከፍተኛ ገቢ እያስገኘ መሆኑ ተነስቷል፡፡ ይኽም ሆኖ፣ ከሠራተኞች ደመወዝ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ጋር የሚነሱት ጥያቄዎች መፍትሔ ሊያገኙ እንደሚገባ ቋሚ ኮሚቴው አሳስቧል የፓርኩ ዋና ሥራ አሥኪያጅ አሕመድ ሰኢድ በበኩላቸው፣ የኢንዱስትሪ ፓርኩ ከተከፈተ ጊዜ አንስቶ በርካታ ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ መግባታቸውን እና በዚኽ የተነሳም ባለፉት ሰባት ዓመታት ውስጥ ሰባት ሺህ ለሚጠጉ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩን ለቋሚ ኮሚቴው አስረድተዋል፡፡

[1]ኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ "'ሚዲያው ተወዳዳሪ፣ ተደማጭና ተአማኒነት ያለው የመረጃ ምንጭ ለመሆን የጀመራቸው ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው' ቋሚ ኮሚቴው።" https://web.facebook.com/share/p/1FSvBHVEkW/

## 4.2.2 የመስክ ጉብኝቶች

በወርሃ መጋቢት፣ የኢትዮጵያ እንደራሴዎች ወደ መስክ ወርደው ሰፋ ያሉ አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ጉብኝቶች አድርገዋል፡፡ መጋቢት መገባደጃ ላይ ወደ ሐረሪ ክልል ጎራ ያሉት የምክር ቤቱ የውኃ፣ መስኖ፣ ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባላት፣ በክልሉ በሚየ ወረዳ የሚገኘውን የንጹሕ መጠጥ ውኃ ፕሮጀክትን ጎብኝተዋል፡፡ ኮሚቴውን የመሩት እንደራሴው ወልደየስ ደበበ፣ በከተማዋም ሆነ በዙሪያዋ እየጋጠመ ያለው የንጹሕ መጠጥ ውኃ ዕጥረት በአስቸኳይ መፍትሄ እንዲያገኝ አሳስበዋል ተብሏል፡፡ ከዚኽ በተጨማሪም ኮሚቴው፣ የፕሮጀክቱ የግንባታ ሥራ ዘጠና ስምንት በመቶ የተጠናቀቀ ቢሆንም፣ ፕሮጀክቱ በተያዘለት ጊዜ ተጠናቆ አገልግሎት መስጠት ባለመጀመሩ ስጋት እንዳለው ለክልሉ ተወካዮች አንስቶላቸዋል፡፡

ከዚኽ የመጠጥ ውኃ ፕሮጀክት በተጨማሪም፣ በተለይም የፍሳሽ ማስወገጃ ግንባታ ፕሮጀክቱ የሥራ ክንውን ገና ስድስት በመቶ ላይ የሚገኝ መሆኑን የተገነዘበው ቋሚ ኮሚቴው፣ ፕሮጀክቱ ከተያዘለት ጊዜ በእጅጉ መዘግየቱ እንዳሳሰበው ለከተማይቱ ተወካዮች ጠቅሶላቸዋል ተብሏል፡፡

በእንደራሴዎቹ ምክር ቤት ምክትል አፈ-ጉባኤ ሎሚ በዶ እና ከምሥራቅ ሸዋ የተወከሉ እንደራሴዎች በሎሜ እና ቦራ ወረዳ ተገኝተው ያደረጉት የመስክ ጉብኝት ደግሞ ሌላኛው የምክር ቤቱ የመጋቢት ወር ዓይነተኛ ክንውን ነበር፡፡ እንደ ምክር ቤቱ ዘገባም፣ ምክትል አፈ-ጉባኤዋ እና እንደራሴዎቹ፣ የተሠሩትን ጨምሮ በመሠራት ላይ የሚገኙትን የበጋ ስንዴ እና የሙዝ ክላስተር የግብርና የልማት እንቅስቃሴዎችን ብቻም ሳይሆን፣ አዲሱን የገጠር ቀበሌዎች አደረጃጀት ጽሕፈት ቤቶችን እንቅስቃሴ ጎብኝተዋል ተብሏል፡፡

በተጠቀሰው መጋቢት ወር የመጎብኘት ዕድል ካገኙት ፕሮጀክቶች መካከል ሊጠቀስ የሚችለው፣ የኮይሻ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት ሲሆን፤ በምክር ቤቱ የመንግሥት ዋና ተጠሪ ሚኒስትር ተስፋዬ በልጅጌ እና ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት የሥራ ኃላፊዎች ጉብኝቱ ተመርቷል፡፡ የኮይሻ ኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ ፕሮጀክት ግንባታ ስድሳ አምስት በመቶ መድረሱም ታውቋል፡፡

በ2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዩሮ ወጪ እየተገነባ የሚገኘው ይኽ ፕሮጀክት፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል በኮንታ ዞን ኮንታ ኮይሻ ወረዳ እና በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ ዞን መሎ ኮዛ ወረዳ መካከል ላይ እንደመገኘቱ፣ ልማቱ የኹለቱን ክልሎች ሕዝቦች ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን በሚፈታ መልኩ እየተገነባ እንደሚገኝም ከመስክ ጉብኝቱ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤቱ የተለያዩ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ የመጋቢት የመስክ ጉብኝቶቻቸው፣ የልማት ዕቅዶችን የት መድረስን ብቻ ሳይሆን፣ በተፈጥሮ አደጋ ከመኖሪያቸው ተፈናቅለው የነበሩ ዜጎች አኹን ያለቡትን ኹኔታም አደጋዎቹ ደርሰውባቸው በነበሩባቸው አካባቢዎች ተገኝተው ተመልክተዋል፡፡ በእንደራሴዋ ፋንታዬ ለገሰ የተመራው የምክር ቤቱ የውጪ ግንኙነት እና የሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ቡድን፣ የተፈጥሮ አደጋው ያስከተለውን ውድመት እና ውድመቱ የመጣውን ዳፋ ለመመለስ የተሠሩ ሥራዎችን አስመልክቶ፣ የከፋ ዞን አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን የቀረበለትን ሪፖርት አድምጧል፡፡ ከሪፖርቱ ማድመጥ እና ከመስክ ምልከታው በኋላም ቋሚ ኮሚቴው፣ በተፈጥሮ አደጋ ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ ዜጎች መሠረተ ልማት ማሟላት እንደሚገባ አስገንዝቧል ተብሏል፡፡ ከዚኽ በተጨማሪም ኮሚሽኑ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ከፋ ዞን በመሬት መንሸራተት የተነሳ ሐምሌ 2016 ዓ.ም. እና ጥቅምት 2017 ዓ.ም. በዴቻ እና አድዮ ወረዳ የደረሰውን አደጋም እንዲኹ ለቋሚ ኮሚቴው አባላት አብራርቷል፡፡ በዚያ የመስክ ጉብኝት ወቅትም፣ በአደጋው ሳቢያ ከቀያቸው የተፈናቀሉት ዜጎች፣ የፌዴራል መንግስቱ በቀጣይ በቋሚነት የምንሰፍርበት ቦታ አዘጋጅቶ መልሶ ያቋቁመን ሲሉ ጠይቀዋል ተብሏል፡፡

[1] የኢፌድሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ “የኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ እያሳየ ያለው ዕድገት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ ተመላከተ” https://web.facebook.com/share/p/1NPvnJEEJ2/

## 5. የፓርላማ ዲፕሎማሲ

በመጋቢት ወር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ካከናወናቸው ሁለት የዲፕሎማሲ ስራዎች የኢትዮጲያና ኩባን ታሪካዊ ግንኙነትና ወዳጅነት እንዲሁም በዲፕሎማሲና በህዝብ ለህዝብ ግንኙነት የበለጠ አጠናክሮ ለመቀጠልና እንዲሁም የኩባ ባለሀብቶች በኢትዮጲያ መዋዐለንዋያቸውን በሚያፈሱበት ጉዳዮች ላይ የኢፌዴሪ የሕ/ተ/ም/ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎና የበኢትዮጲያ የኩባ አምባሳደር መይሲን ሱዋሬዝ አልቫሬዝ ውይይት ማድረጋቸው አንደኛው ነው፡፡ በተጨማሪም የኢፌዴሪ የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ አገኘሁ ተሻገር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስቴር የተከበሩ ዶ/ር ተስፋዬ በልጅጌ በኡዝቤኪስታን በተካሄደው የአለም ዓቀፍ ፓርላማ ህብረት (Inter-Parliamentary Union-IPU) የጋራ መድረክ ላይ ተሳትፈዋል፡፡ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች፣ ሰላም ግንባታ፣ ዘላቂ ልማትና ፍትሀዊ ተጠቃሚነት፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና የመሳሰሉት አጀንዳዎች የህብረቱ የመወያያ አጀንዳዎች ነበሩ፡፡

በዚሁ መድረክ ላይ የተሳተፉት ሌላው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ ዶ/ር ምረቱ ሻንቆ ‘የነገን የአለም መሪዎችን ማፍራት’ /Cultivating the Next Generation of Global leaders/ በሚል ርዕስ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡ በንግግራቸውም ወጣቶችን ያላማከለ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ቀጣይነት እንደማይኖረው ገልፀው በተጨባጭ የወጣቶችን ተሳትፎና ሚና ማሳደግ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

## 6 የብሪፍ እይታዎች

### 6.1 በአዋጅ ቁጥር 1373/2017 ላይ የተደረገ ሐተታዊ ምልከታ

የፌደራል መንግስት በክልል ጣልቃ የሚገባበትን ሥርዓት ለመደንገግ የወጣው አዋጅ ቁጥር 359/1995 መሰረት በማድረግ የፌደራል መንግስቱ በትግራይ ክልል ጣልቃ በገባበት ወቅት ባጋጠሙ ችግሮች ላይ በመንተራስ የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማድረግ አዋጅ ቁጥር 1373/2017ን አፅድቋል። ቀዳሚው አዋጅ በድህረ-ጊዜያዊ አስተዳደር የሚያጋጥሙ ህጋዊና ፖለቲካዊ ክፍተቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አልነበረም።

አዋጅ ቁጥር 1373 የፌዴሬሽን ም/ቤትንና የፌዴራል መንግስቱን ተቋማዊ አቅም በመገንባት በተለይም የፌዴራል መንግስቱ በትግራይ ክልል የጣልቃ መግባቱ ጊዜ ሲገባደድ ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት የህግና ፖለቲካዊ እጥረቶችን ለመድፈን አይነተኛ ሚናን ይጫወታል። በሌላ በኩል በትግራይ ክልል ካጋጠመው ሁኔታ በመነሳት የፖለቲካ ቡድኖች የበላይነትን፣ የጊዜያዊ አስተዳደሩ በልማትና አስተዳደር ዘርፍ ስለሚጫወተው ሚናና ተያየዥ ጉዳዮች እንዴት እንደሚፈቱ አሁንም ግልፅ አይደለም።

በመሆኑም ይህ ሃተታዊ ምልከታ የቀዳሚውን አዋጅ ውሱንነቶች፣ በትግራይ ክልል ስላጋጠመው የህግና የፖለቲካ እውነታ፣ የተሻሻሉ ጉዳዮችንና እንድምታዎችን ይፈትሻል።

### የአዋጅ 359/1995 ውስንነቶች

የኢትዮጵያ የፌዴራል አወቃቀር በ 1995ቱ ሕገ-መንግስት በዝርዝር እንደተቀመጠው የህዝቦች ራስን በራስ የማስትዳደር መርህ ላይ የተመሰረተ ነው። የህዝቦች ማንነትና ራስን ማስተዳደር ከፍተኛ ስፍራ የተሰጣቸው የሕገ-መንግስታዊ አካሎች ናቸው። አዋጅ 359 ያስፈለገውም በአንድ ክልል ውስጥ የሚፈጠሩ ቀውሶች ማለትም የህገ-መንግስታዊ ስርዓት አደጋ ላይ መውደቅ፣ የብሔራዊ ሉዓላዊነት አደጋዎች ሲፈጠሩና የእርስ በርስ ግጭቶች በሚፈጠሩበት ጊዜ የፌዴራል መንግስት በፌደሬሽን ም/ቤት ውሳኔ መሰረት ጣልቃ እንዲገባና ሠላማዊ ሥርዓት እንዲመለስ አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው።

ነገር ግን አዋጁ የጊዜያዊ አስትዳደርን ቆይታን በሁለት አመት ብቻ በመገደቡና ሁሉም ችግሮች በዚህ ጊዜ ውስጥ ይፈታሉ ብሎ ማመኑ የሚከተሉት ውስንነቶች የታዩበታል።

የአዋጁ አንቀጽ 15 ቀጥር 3 የፌዴሬሽን ም/ቤት የክልሉ ችግር አልተፈታም ብሎ ካመነ የመቆያ ጊዜውን ከስድስት ወራት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ የማራዘም ስልጣንን ይሰጠዋል። ይህ ደግሞ የክልሉን ነባራዊ ሁኔታ ያገናዘበ ሆኖ አልተገኘም።
የፌዴሬሽን ም/ቤት በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ የሚሰበሰብ በመሆኑ አስቸኳይ ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን በተጨባጭ ያዘገይል። በክልሎች የሚፈጠሩ ቀውሶች ውሳኔ እስከሚሰጣቸው ድረስ ሊባባሱ እንደሚችሉ ይገመታል።

እነዚህ ከላይ የተመለከቱት ችግሮች በትግራይ ክልል እስከተዩበት ጊዜ ድረስ በንድፈ-ሃሳብ ደረጃ ብቻ የነበሩ ሲሆን ተግባራዊ መሆናቸው ስለተረጋገጠ የአዋጁን ማሻሻያ እውን አድርጐታል።

## በትግራይ ያጋጠመው ሁኔታ

የፌዴራል መንግስቱ ሕወሀትን የፌዴራል የጦር ሠፈርን በማጥቃት ከወነጀለበትና ሕወሀት መራሹን ክልላዊ መንግስት አስወግዶ ጊዜያዊ ክልላዊ መንግስት አዋቅሮ ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ህግ-ነክ ጥያቄዎች ሲነሱ ቆይተዋል። ጊዜያዊ አስተዳደሩ ያለውጤት የቆይታ ጊዜውን ካገባደደ፣ የፌዴሬሽን ም/ቤት እስኪሰበሰብ ማን ውሳኔ ይሰጣል፣ ፈጣን እርምጃዎችን እንዴት ይወሰዳሉ፣ በትግራይ ያሉት የፖለቲካ ሐይሎች ግጭት ውስጥ ባሉበት ሁኔታ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንዴት መመለስ ይቻላል የሚሉት ጥያቄዎች ጥቀቶቹ ናቸው።
እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ችግሮች ከመሬት ላይ የተገኙ እውነታዎች ስለሆኑ ከአዋጅ 359 የህግ-ማዕቀፍ የሚያስወጡና መንግስትም ተግባራዊ ዕርምጃዎችን እንዲወስድ አስገድደውታል። ይህም በአዋጁ መንፈስና በተጨባጭ ፖለቲካው መካከል ያሉትን ልዩነቶች አጉልቶ አሳይቷል።

በመሆኑም አዋጅ 1373/2017 ችግርን ለመቅረፍ አስቀድሞ በተወሰዱ እርምጃዎች አማካኝነት የተቀረፀ የማሻሻያ ህግ ነው። እንዲህ አይነት የህግ አወጣጥ ዘዴዎች አልፎ አልፎ የሚደረጉና የችግሮችን መባባስ ለመከላከል ጥቅም ላይ የሚውሉ ቢሆንም የህግን ተገማችነትና ህገ-መንግስታዊ ምሉእነትን እንዳይሸረሽረው መጠንቀቅ ያሻል።

ህጎች በሚወጡበት ጊዜ መጪውን ጊዜ የሚገምቱ እና እንደየሁኔታው መሻሻል የማያስፈልጋቸው ከመሆኑም በላይ፣ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት ያሏቸውን ስልጣን በአግባቡ እንዲወጡ የሚያበረታታ መሆን አለበት ።

## የማሻሻያ ይዘቶች

### ለፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ ተጨማሪ ስልጣን ስለመስጠት

የፌዴሬሽን ም/ቤት በአመት ሁለት ጊዜ ብቻ የሚሰበሰብ ሲሆን በክልሎች የፌዴራል ጣልቃ-ገብነትን የሚጋብዙ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ-ጉባኤው የፌዴራል መንግስቱን ለማዘዝ የሚያስችል ስልጣን በዚህ አዋጅ የተሰጠው ሲሆን ጉልህ የሆነ የአዋጁ ማሻሻያ ነው። ይህም በአዋጅ 359 የነበረውን ውስኑነት ቀርፏል። ይህም የፌዴራል ተቋማቱ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ችሎታቸውን አዳብሯል።
የፌዴሬሽን ም/ቤት አባላትም በሚሰበሰቡበት ጊዜ የአፈ-ጉባኤውን ውሳኔ የሚመረምሩና የሚወስኑ በመሆናቸው የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ሕገ-መንግስታዊ በጋራ የመወሰን ስልጣንን ያስጠብቃል። ለጊዜያዊ አስተዳደሮች የሚሰጥ የጊዜ ገደብ

ነባሩ አዋጅ የጊዜያዊ አስተዳደሮች የተመደበላቸው ጊዜ ሲያበቃ ከስድስት ወራት በላይ ማራዘም እንደማይቻል የደነገገ ሲሆን መጠነ ሰፊ ግጭቶች በነበሩባቸውና ውስብስብ የፖለቲካ ሁኔታዎች ባሉባቸው ጊዜያዊ አስተዳደሮች ስድስት ወራት በቂ አለመሆናቸውን በትግራይ ክልል ከነበረው ሁኔታ መረዳት ተችሏል። አዋጅ 1373/2017 ለመጀመሪያ ጊዜ እስከ አንድ አመት ማራዘም እንደሚቻልና አስፈላጊ ከሆነም ለሁተኛ ጊዜ ሊደገም እንደሚችል ደንግጓል።

## የማሻሻያው ጠንካራና ደካማ ጉኖች

- በፌዴሬሽን ም/ቤት ስብሰባ መዝግየት ምክንያት የመንግስትን ሕገ-መንግስታዊ ውበቶችን የማስከበር ኃላፊነት እንደወጣ ለማድረግ አፋጣኝ ሁኔታ መፈጠሩ
- የጊዜያው አስተዳደሮች ከግጭት የመውጫ ጊዜ ከስድስት ወራት የማራዘሚያ ጊዜ በላይ ሊያስፈለገው ስለሚችልበትና ይህም መፈቀዱ
- በአፈ-ጉባኤው ውሳኔና በፌዴሬሽን ም/ቤት አባላት የመሰብሰቢያ ጊዜ መሀል ያለው ክፍተት ተጠያቂነትን የሚያላላ መሆኑ
- የጊዜያዊ አስተዳዳሮች የመቆያ ጊዜ በተራዘመ ቁጥር በህዝቦች ማንነት ፖለቲካ ላይ የተመሠረተውን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አወቃቀር በተለይም የክልል ራስ ገዝ አስተዳደርን የማዳከም ስሜት ሊፈጥር ይችላል። ሕጋዊ ትክክለኛነት ቢኖረውም የፖለቲካ ስሜቶችንእንደሚያጎላ ደግሞ ያሰጋል።

## እንድምታዎች

የተሻሻለው አዋጅ 1373/2017 ዓ.ም የአዋጅ 359ን ውስንነቶች በቀረፈ መልኩ ወደስራ ገብቷል። ኢትዮጵያ የፌዴራላዊ ሞዴሏ ፖለቲካዊ ቀውሶች ሲገጥሙት እንደው የችግር መፍቻ ዘዴ ሆኖ ይቀጥላል። በተቀመጠለት መንፈስ ከተተገበረ ሕገ-መንግስታዊ አስተዳደርን ለማስከበር ይረዳል። ይህ ካልሆነ ግን የአሳታፊና የብዙሀን ሞዴልን ይዞ የተነሳዉን ሕገ-መንግስት ይሸረሽራል።

ህጉ ብቻውን ውጤት መሆን ስለማይችል በትክክል ከተተረጐመ፣ ተቋማዊ ለውጦችን ማምጣናት መተግበር ከተቻለ ብቻ ነው ተጨማሪ ማራዘሚያዎችን ማስቀረት የሚቻለው ይህንንም ለማረጋገጥ አንዳንድ እርምጃዎችን መውሰድ ተገቢ ነው። የክትትልና የቁጥጥር ዘዴዎችን መንደፍና መተግበር እንዲሁም የጊዜያዊ አስተዳደሮችን የአፈፃፀም መመዘኛዎች በግልጽ ማስቀመጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

## መደምደሚያ

የአዋጅ 1373/2017 መጽደቅ ሀገራዊ አንድነትንና ሥርዓትን፣ ፌዴራላዊ ብዝሀነትንና ያልተማከለ አስተዳደርን ለማረጋገጥ ነባራዊ ህጐችን በማሻሻል ጭምር መስራት እንደሚያስፈልግ አሳይቷል። አዋጁ ክፍተቶችን ለመሸፈን ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም ውጤታማነቱ የሚረጋገጠው ግን በምናራምደው የፖለቲካ አቋም ብቻ ነው።

የህገ-መንግስቱ መሠረታዊ ዕሴቶች የሆኑትን ራስን በራስ የማስተዳደርና በጋራ የመወሰን አቅምና ስልጣን እንዳይሸረሸሩና የጊዜያዊ አስተዳደሮቹን እንዲሁም የመንግስትን ጣልቃ-ገብነት ጊዜያዊነቶችን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ይህ እንዲሳካ ሥልጣንና ተጠያቂነት የማይነጣጠሉ ማድረግ ተገቢ ነው። ጠንካራና በመርህ ላይ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም የሚተገበረው በዚህ መንገድ ብቻ ነው።

## 6.2 የመስክ ስራዎች እይታ

በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አባላት በምርጫ ክልላቸው ከሚገኙ መራጮችና ተቋማት ጋር በቀጥታ በመገናኘት ስለተከናወኑና በመከናወን ላይ ያሉ የልማት እንቅስቃሴዎችንና ፈተናዎችን በማየት መረጃ ያገኙበትና ሕገ መንግሥታትዊ ኃላፊነታቸውን ከመወጣት ባሻገር የመንግሥትንና የሕብረተሰብን ግንኙነት ወደ ተሻለ ከፍታ እየወሰዱበት ያለ ሂደት ነው፡፡

በመጋቢት ወር ኮይሻ የኃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድብና የኮምቦልቻን የኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዲሁም ከግብርና እስከ መሰረተልማት እና አደጋ መከላከልና የመንግሥት አገልግሎትን እስከ ማሻሻል ያሉትን ያካተተ ሲሆን ቋሚ ኮሚቴዎች የሚያደርጊቸውን ምልከታዎች ሙሉ ስዕል እንዲኖራቸው የሚያደርግ ነው፡፡ የመስክ ምልከታቸው በቅርብ ከሚያገኙት አዲስ አበባ ጀምሮ ራቅ ያሉትን እስከ ከፋና ጋሞ ዞኖችን ያካተቱ ነበሩ፡፡

በተጨማሪም አንድ ተወካይ በአሜሪካ ሚኒሶታና ኦሀዮ ግዛቶች በመገኘት ከዲያስፖራ ማህበረሰብ መሃል በመገኘት ጉብኝት ማድረጉን ጽፈት ቤቱ ዘግቧል፡፡

በዚህ አንቀጽ የብሪጅ እይታ በኮምቦልቻ የኢንደስትሪ ፓርክ ጉብኝትን እንደ ለዓብይነት ያነሳል፡፡ ምንም እንኳን ተወካዮች የውክልና ሥራዎቻቸውን በዚህ መልኩ እየተወጡ ቢሆንም በመስክ እይታ ወቅት ለሚያጋጥሟቸው ችግሮች የመፍትሄ አካል ለመሆን የክትትል ስርዐት መከተል ያስፈልጋቸዋል፣ ስርዓቱ ካለም ከህዝብ ግልጽ መሆን እና ምልከታው ያስከተላቸው ለውጦችን ይፋ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በሌሎች ሀገሮች ለምሳሌ በኬንያ እንደራሴዎች ከህዝብ ጋር ከሚያገናኟቸው መድረኮች በተጨማሪ የምርጫ ክልሎች ቢሮዎች ያሏቸው ሲሆን ቅሬታዎችን የሚቀበሉና ፕሮጀክቶችን የሚከታተሉ ሰራተኞች አሏቸው፡፡ በተጨማሪም የዲጂታልና የማህበራዊ ሚድያን በመጠቀም ከመራጩ ጋር የሚገናኙ ሲሆን አንዳንድ የፓርላማ አባላት በአካባቢው ስላሉ ፍላጎቶች ወይም በሂደት ላይ ባሉ ፕሮጀክቶች እርካታን በተመለከተ የተዋቀረ ግብረ መልስ ለመሰብሰብ የመነሻ ጥናቶችን ያካሂዳሉ፡፡

ተወካዮች የተመለከቷቸው እንደዝቅተኛ ክፍያና ያልተሟላ የኑሮ ሁኔታ ማሳሰቢያ ከመስጠት ባሻገር በክትትል ስርዐት በመደገፍ ውጤታማ ክትትል ማድረግ ይገባቸዋል፡፡

ከአራት አመት በፊት የተሰራው የአለም ባንክ ጥናት እንደሚያሳየው በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚከፈለው ክፍያ ከአካባቢው የመሠረታዊ ፍላጎቶች ወጪ ጋር ሲነፃፀር በሌሎች የሀገር ውስጥ ኢኮኖሚ ዘርፎች ከሚከፈለው ክፍያ ከሚከፈለው ክፍያ ጋር ተመሳሳይ ነበር፡፡ የተለያዩ ጥናቶች አከራካሪ መረጃዎችን ቢያመላክቱም፤ ይህ የአለም ባንክ ጥናት የሰራተኞች ጠቅላላ የክፍያ ፓኬጅ አማካኝ በአካባቢያዊ የድህነት መስመር ሲለካ ከሚቀመጠው ዋጋ በአራት እጥፍ ገደማ የሚበልጥ መሆኑን ያሳያል፡፡

ነገር ግን ጥናቱ የማካካሻ እና የክፍያ መዋቅር በኢንዱስትሪዎች መሃል በእጅጉ መለያየት እና በቂ የሆነ መረጃ ያለመኖር እንደ ችግር ይታያል፡፡በተለይ ደግሞ በአሁን ውቅት የገንዘብ የመግዛት አቅም እና የምግብ ዋጋ ንረት ጋር ተያይዞ ይህ የኢንዲስትሪ ፓርክ ሰራተኞች በምን መንገድ ኑሯቸው ታውኳል

ከሚለው አስፈላጊ ጥያቄ በተጨማሪ የአካባቢ የድህነት ጣራ ውሰና፣ የሰራተኛ ደሞዝ የገቢ ግብር ሁኔታ፣ ለኢንዱስትሪ ዘርፉ ስለሚደረገው ጥበቃ እና የኢንዱስትሪ ፓርክ ሰራተኞች ስላሏቸው የመደራጀት እና መብታቸውን የመጠየቅ መብት ዝርዝር ትንተና ላይ በመመርኮዝ የመስክ ጉብኝቶች ሊመሰረቱ ይገባል፡፡

በተጨማሪም ለጉብኝት ተወካዮች በሚሄዱባቸው ወቅቶች ማብራርያ የሚሰጧቸው ግለሰቦች እና ተቋማት እንዴት እና ለምን ይመረጣሉ የሚል ፣ማብራርያ ለመራጮች ግልጽ መሆን አለበት፡፡ አሁን ባለው የምልከታ ሽፋናቸው አዎንታዊና አሉታዊ ጉዳዮችን በሙሉ መዳሰስ የሚያስችል አቅም ስለማይኖራቸው ለፖሊሲ ግምገማ እና መሻሻል ሊያደርጉት የሚችሉትን አስተዋጽዎ ይገድብባቸዋል፡፡

ከተቋማት ጋር የሚደረጉ የመስክ ምልከታዎች ከታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ከሚደረጉት የተለያዩ ውጤት ስለሚኖራቸው የምልከታችውን አድማስ በማመጣጠንና በማቀናጀት አገራዊ ፋይዳ ያላቸውን ፖሊሲዎችንና ህጎችን ለመቅረጽ/ለማሻሻል መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡

[1] Parliament of Kenya. "Members Services and Facilities Committee collect views from constituency offices' staff" http://parliament.go.ke/members-services-and-facilities-committee-collect-views-constituency-offices-staff

[1] World Bank Group. 2021. Wages and compensation in Ethiopia's industrial parks: evidence from a firm survey. https://documents1.worldbank.org/curated/en/834531617685578320/pdf/Wages-and-Compensation-in-Ethiopia-s-Industrial-Parks-Evidence-from-a-Firm-Survey.pdf

## በመሆኑም ብሪጅ ሪሰርች ኤንድ ኢኖቬሽን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀርባል።

1 ተወካዮች የቁጥጥር ሥራቸውንና የፖሊሲና የህግ ማውጣት ተፅኖዎቻቸውን ለማጎልበት የሚረዷቸውን የተደራጁ የክትትል ማዕቀፎች ያስፈልጓቸዋል፡፡ በተጨማሪም የሚያቀርቧቸውን የፖሊሲና የአሰራር እና የህግ ማሻሻያዎችን ሪፖርት ከማድረግ ባሻገር በተግባር እንዲውሉ ተፅእኖ በማድረግ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

2 ተወካዮች ከመደበኛ የመስክ ምልከታ ባሻገር በርካታ ሀሳቦች የሚገኙባቸውን የማህበረሰብ ውይይቶች በማዘጋጀትየታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ድምጾች በፖሊሲና በህግ ማሻሻያ/ቀረጻ እንዲካተቱ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

3 ተወካዮች ማህበራዊ ተጠያቂነትን ማስፈንየሚችሉ ፕሮጀክቶች እንዲስፋፉ ጥረት ማድረግ የሚገባቸው ሲሆንበህዝብ ተሳትፎ የሚገኙትን የልማት ግብረመልሶች ግልጽነትን፣ ተጠያቂነትንና መተማመንን ከማስፈን ማናቸውባሻገር ለፖሊሲና ለህግ ግብዐት እንዲሆኑ ማስቻል ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ከአለም አቀፍ ተቋማትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ያላቸውን አጋርነት ማጠናከር ያስፈልጋቸዋል፡፡

እንደራሴዎች ያደረጓቸው የመስክ ምልከታዎች ዘርፈ ብዙና የተለያዩ ዘርፎችን ወደ አንድ ማዕከል በማምጣት የፖሊሲና ለህግ የማውጣት ስራ ግብዓት በመሆን ያገለግላሉ፡፡ ከዚህ የሚገኘውን ጥቅምና የተወካዮች ተፅእኖ በከፍተኛ ደረጃ ለማሳደግ እንደራሴዎች ከታችኛው የህብረተሰብ ክፍል ጋር ያላቸውን ትስስር ማጎልበት፣ የፖሊሲና የህግ ማውጣት ተጽእኖዋቸውን ማጠናከርና ጠንካራ የሆነ የክትትል ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህ ሲሆን ብቻ ነው ኢትዮጵያውያን በተወካዮቻቸው አማካኝነት ፍላጎታቸውንና ተስፋቸውን አካታች፣ ውጤታማና ዘላቂ በሆነ መንገድ ሠላምን፣ ልማትንና ብልፅግናን ማምጣት የሚቻለው፡፡

BRIDGE Research & Innovation

Parliaments, Policy, Peace

BRIDGE
Research & Innovation